የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No. 27
ADDIS ABABA, 3rd June, 2021

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፮/፪ሺ፲፫

የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ማሻሻያ አዋጅ........................ ገጽ ፲፫ሺ፪፻፶፮

Content

Proclamation No. 1246/2021

Ethiopia's Overseas Employment Proclamation Amendment ……………………………Page 13256

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፮/፪ሺ፲፫

## የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ማሻሻያ አዋጅ

የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፮/፪ሺ፲፫» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ማሻሻያ

የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፬) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፲፭)፣ (፲፮)

## PROCLAMATION NO. 1246/2021

## ETHIOPIA'S OVERSEAS EMPLOYMENT AMENDMENT PROCLAMATION

**WHEREAS**, it has become necessary to amend Ethiopia's Overseas Employment Proclamation No. 923/2016;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Ethiopian's Overseas Employment (Amendment) Proclamation No. 1246/2021."

### 2. Amendment

The Ethiopian's Overseas Employment Proclamation No. 923/2016 is hereby amended as follows:

1/ The following new Articles (15), (16), (17) and (18) are added after Sub-Article (14) of

ያንዱ ዋጋ Unit Price 22.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

(፲፯) እና (፲፰) ተጨምረው ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (፲፭) እና (፲፮) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጾች (፲፱) እና (፳) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

"፪(፲፭) "የተጎጂ ሠራተኛ ተወካይ" ማለት በሕግ አግባብ ውክልና የተሰጠውና የወካዩን ማናቸውም ጉዳይ የሚከታተል ሰው ነው፡፡

፪(፲፮) "ሌበር አታሼ" ማለት በተቀባይ ሀገር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ተመድቦ ለሥራ የተሰማሩ ዜጎችን መብት፣ ደህንነት እና ክብር ተጠብቆ እንዲሰሩ የሚከታተልና ድጋፍ የሚሰጥ ሠራተኛ ነው፡፡

፪(፲፯) "የመግባቢያ ሰነድ" ማለት የውጭ ሀገር የሥራ ቅጥርን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በተቀባይ ሀገር መንግስት ወይም በተቀባይ ሀገር ከሚገኝ አሠሪ ጋር የሚደረግ የጋራ መግባቢያ ስምምነት ነው፡፡

፪(፲፰) "የቤት ውስጥ ሥራ" ማለት ከአሠሪው ጋር በሚደረገው የሥራ ቅጥር ውል መሠረት ለሚከፈል ክፍያ በቤት ውስጥ የሚከናወን ማንኛውም ዓይነት ሥራ ነው፡፡"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፫ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፫ ተተክቷል፡-

"፫/ <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

አዋጁ በመንግሥታዊ አካል፣ በኤጀንሲ እና በቀጥታ በሚደረግ ቅጥር ኢትዮጵያዊያን በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ግንኙነት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡"

Article (2) of the Proclamation and the existing Sub-Articles (15) and (16) are re-numbered as Sub-Articles (19) and (20) respectively.

"2(15) "Representative of Victim Worker" means any person who has the legal authority to represent the principal and act on any matters on the behalf of the principal.

2(16) "Labour Attaché" means an officer assigned by the Ministry in counsultation with Minstry of Foreign Affairs and deployed at a receiving country with the duty of monitoring and providing support in ensuring the protection of the rights, safety and dignity of Ethiopians employed overseas.

2(17) "Memorandum of Understanding" means an agreement concluded between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia with receiving country or with employer located in receiving country pertaining to overseas employment.

2(18) "Domestic work" means any kind of household work done with payment by concluding a contract of employment with the employer."

2/ Article 3 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 3:

"3/ **<u>Scope of Application</u>**

This Proclamation shall apply to overseas employment relation of Ethiopians conducted by public employment organs, agency and by direct employment."

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተተክቷል፡-

"፯/ ስለ ትምህርት ደረጃ እና ሙያ ብቃት ምዘና

፩/ ለቤት ውስጥ ሥራ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄድ ማንኛውም ሠራተኛ፡-

ሀ) በሚቀጠርበት የሥራ መስክ ስልጠና ወስዶ አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው፣

ለ) በውጭ ሀገር ሲሰራ ቆይቶ ወደ ሀገር ቤት የተመለሰ ከሆነ በሚቀጠርበት የሥራ መስክ ስልጠና መውሰድ ሳያስፈልገው አግባብ ባለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው፤

፪/ የሰለጠነ የሰው ኃይል በውጭ ሀገር ሥራ ላይ ሊሰማራ የሚችለው፡-

ሀ) የሥራ መደቡ የሚጠይቀውን የትምህርት ዝግጅት፣ የሙያና የሥራ ልምድ የሚያሟላ፣

ለ) በሚቀጠርበት የሥራ መስክ እንደአስፈላጊነቱ አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው መሆን አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሠራተኛው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚጠየቀው አሠሪው የሚጠይቃቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡"

3/ Article 7 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article.

"7/ **Level of Education and Occupational Competence Assessment**

1/ Any worker who desires to take up overseas employment for domestic work shall:

a) be trained and possess a certificate of occupational competence issued by the appropriate competence assessment center for the work he is to be employed;

b) a worker who has been previously working overseas and has returned shall possess a certificate of occupational competence issued by the appropriate competence assessment center for the work he is to be employed without training;

2/ skilled worker who desires to take up overseas employment shall:

a) fulfill the necessary educational competence and work experience required for the work;

b) possess as necessary a certificate of occupational competence issued by the appropriate competence assessment center for work he is to be employed.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the worker shall be required to present certificate of occupational competence only when it is ascertained that he fulfills the other requirements set by the employer."

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

፬/ ከአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፡-

"፲(፭) ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተደነገገው ቢኖርም በማሻሻያ አዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በኤጀንሲ አማካኝነት ለሥራ የተሰማራ ቤት ሠራተኛ ያልሆነ በውጭ ሀገር ያለው አሠሪ ለኤጀንሲው የሚገባውን ክፍያ የማይሸፍን መሆኑ በሚያደርጉት የሥራ ስምሪት ስምምነት ያልተመላከተ ከሆነ ተቀጣሪው ሠራተኛ እስከ አንድ ወር ደመወዙን በአራት ጊዜ የሚከፈለው ይሆናል፡፡"

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፪ ተተክቷል፡-

"፲፪/ <u>የሁለትዮሽ ስምምነት ወይም የመግባቢያ ሰነድ ስለማስፈልጉ</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት ሠራተኛን በውጭ ሀገር ለሥራ ማሰማራት የሚቻለው፡-

፩/ ለቤት ውስጥ ሥራ እንደ ተቀባይ ሀገር የሕግ አግባብ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተቀባይ ሀገር መካከል የሁለትዮሽ ስምምነት ወይም መግባቢያ ሰነድ ሲኖር፤

፪/ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለሚፈልግ ሥራ እንደ አግባቡ በሚኒስቴሩ እና በተቀባይ ሀገር ከሚገኘው አቻ ሥልጣን ካለው የመንግስት ተቋም ወይም እውቅና ካለው አሠሪ ኩባንያ የሁለትዮሽ ስምምነት ወይም መግባቢያ ሰነድ ሲኖር ነው፡፡

4/ The following new Sub-Article (5) is added after Sub-Article (4) the Article of 10 of the Proclamation.

"10(5) Notwithstanding the provision of Sub-Articles (1) to (4) of this Article, according to Article 7 Sub-Article (2) of the amendement proclamation, any worker, who is employed overseas through employment agency, other than in domestic. work shall pay the employment agency the amount of his upto one month salary over four payment period.

5/ Article 12 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 12.

"12/ **<u>Requirement of Bilateral Agreement or Memorandum of Understanding</u>**

In accordance with this Proclamation, deployment of workers for overseas employment shall be effected:

1/ For domestic work, in accordance with the legal framework of the receiving country, if there is bilateral agreement or memorandum of understanding concluded between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and receiving country;

2/ For skilled workers, if there is memorandum of understanding or bilateral agreement concluded between the Ministry and competent government authority or accredited employing company in the receiving country.

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

፫/ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚሰማራበትን ሥራ አፈላልጎ ያገኘ ኤጀንሲ በተቀባይ ሀገር መንግስት እውቅና ካለው ቀጣሪ አሠሪ ኩባንያ ጋር የሥራ ስምሪት ስምምነት እንዲፈፅም ሚኒስቴሩ የተቀጣሪ ዜጎች መብትና ደህንነት የሚጠበቅ መሆኑን በማረጋገጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡"

፮/ የአዋጅ አንቀጽ ፲፭ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፭ ተተክቷል፡፡

"፲፭/ <u>ቦርድ ስለማቋቋም</u>

፩/ የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ቦርድ (ከዚህ በኃላ ቦርድ እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ማሻሻያ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የቦርዱ ዓላማ አግባብነት ያላቸውን ባለድርሻ መሥሪያ ቤቶችን በማስተባበርና በማቀናጀት ወደ ውጭ ሀገር ለሥራ የሚሄደውን ዜጋ መብቱና ደህንነቱ ተጠብቆ ለሥራ እንዲሠማራ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ተጠናክሮ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

፫/ የቦርድ አባላት፡-

ቦርዱ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የሠራተኞና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት የቦርድ አባላት ይኖሩታል፡፡

ሀ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

ለ) የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር፣

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) and (2) of this Article, an agency who managed to get job opportunity for skilled manpower, the government shall give permission to undertake an agreement to do so with receiving country's company upon ascertainment of the right and safety of the employees shall be respected."

6/ Article 15 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 15.

"15/ **<u>Establishment of Board</u>**

1/ Ethiopian Overseas Employment Board (hereinafter Board) is hereby established under this amended Proclamation.

2/ The objective of the Board is to coordinate relevant stakeholders towards strengthening the implementation of overseas employment and ensuring that the rights, safety and dignities of Ethiopians employed overseas are protected.

3/ Members of the Board:-

The Board shall be chaired by the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Labour and Social Affairs and will have the following Board Members:-

a) Ministry of Foreign Affairs;

b) Ministry of Science and Higher Education;

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

ሐ) የጤና ሚኒስቴር፣

መ) የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፡

ሠ) የሥራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን፡

ረ) የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፡

ሰ) የኢምግሬሽን፣ የዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ፡

ሸ) የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፡

ቀ) ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት እንደአስፈላጊነቱ የሚካተቱ ይሆናል፡፡

፬/ የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት እንደሚከተሉት ይሆናል፡-

ሀ) አዋጁ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣

ለ) የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማሰማራት የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣

ሐ) ከሥራ ስምሪት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከተቀባይ ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ወይም የጋራ መግባቢያ ስምምነት የሚደረግበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡

መ) በተቀባዩ ሀገር ውስጥ በዜጎች ላይ የመብት መጣስ ወይም ጉዳት ሲደርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፡

ሠ) ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በሕገ-ወጥ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ድርጊት የሚሳተፉ አካላት ላይ በህግ አግባብ ተገቢው እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤

c) Ministry of health;

d) Attorny General;

e) Job Creation Commission;

f) Federal Police Commission;

g) Immigration Nationality and Vital Events Agency;

h) Federal Technical and Vocational Education and Training Agency;

i) Other Institutions may be included as deemed appropriate.

4/ Powers and Duties of the Board:-

a) follow up, supervise and ensure the proper implementation of this Proclamation;

b) follow up, supervise and ensure, activities enabling the overseas deployment of traind manpower are implemented;

c) facilitate the conclusion of bilateral agreement or memorandum of understanding with receiving countries;

d) in cooperation with relevant authorities, ensure that necessary measures are taken against the violation of Ethiopian workers' rights and abuse in receiving countries;

e) in cooperation with relevant authorities, ensure that participants in an illegal overseas employment activities are brought to justice;

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

ረ) የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት በተመለከተ ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ መፈጠሩን ያረጋግጣል፤

ሰ) የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪትን በተመለከተ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር የሀሳብ ልውውጥ እንዲደረግና የተጠናከረ የመረጃ ማዕከል እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሸ) የራሱን አሰራር መመሪያ ያወጣል፡፡"

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፦

"፳(፪) ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን ማንኛውም ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ መሠረት የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት እየተወጣ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ተቆጣጣሪ ይመድባል፡፡"

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሐ) ተሰርዞ ነባሮቹ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ) እና (ረ) እንደቅደም ተከተላቸው (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ እና (ሠ) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፦

"፳፪(፪) አመልካቹ የንግድ ማህበር ከሆነ የተቋቋመበት ዓላማ በውጭ ሀገር ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ የንግድ ማህበሩ አባላት በሙሉ ኢትዮጵያዊነት ዜግነት ያላቸው እና ከአንድ ሚሊዮን ያላነሰ የኢትዮጵያ ብር የተዋጣ መዋጮ ያለው፡፡"

f) ensure the provision of awareness creation activities concerning overseas employment for public at large;

g) facilitate the exchange of information among relevant stakeholders and the creation of well-established data center on overseas employment;

h) issues its own operational Directives."

7) Sub-Article (2) of Article 20 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2):-

"20(2) The Ministry or competent authority shall assign overseas employment inspectorate to monitor agencies, if they are operating within the ambit of this Proclamation."

8/ Paragraph (c) of Sub-Article (3) of Article 20 of the Proclamation is deleted and previous paragraph (a), (b), (d), (e) and (f) are re-numbered as paragraph (a), (b), (c), (d) and (e).

9/ Sub-Article (2) of Article 22 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2):

"22(2) Where the applicant is a business organization, it shall have objective of overseas employment exchange service and all its members are Ethiopian citizens and have a paid up capital not less than Birr One Million in shares or contributions."

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

፲/ ከአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ(፪) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፫) እና (፬) ተጨምረው ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፫) ንዑስ አንቀጽ (፭) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

"፳፪(፫) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም የሰለጠነ የሰው ኃይል በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ላይ እንዲሰማራ ለማድረግ ከኢትዮጵያዊ ጋር ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ሀገር ዜጋ በኤጀንሲነት ተቋቁመው መስራት የሚችሉት፡-

ሀ) አመልካቹ በሽርክና ማህበር ወይም ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር ወይም በአክስዮን ማህበር የተቋቋመ ድርጅት ከሆነ የአክሲዮን ድርሻ ፸፭ በመቶ (ሰባ አምስት በመቶ) ከኢትዮጵያውያዊ ፳፭ በመቶ (ሃያ አምስት በመቶ) ትውልደ ኢትዮጵያዊ ሆኖ በድምሩ ከሁለት ሚሊዮን ብር ያላነሰ የተዋጣ መዋጮ ያለው፤

ለ) አመልካቹ በሽርክና ማህበር ወይም ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር ወይም በአክስዮን ማህበር የተቋቋመ ድርጅት ከሆነ የአክሲዮን ድርሻ ፹ በመቶ (ሰማንያ በመቶ) ኢትዮጵያዊ፤ ፳ በመቶ (ሃያ በመቶ) የውጭ ሀገር ዜጋ ሆኖ በድምሩ ከሁለት ሚሊዮን ብር ያላነሰ የተዋጣ መዋጮ ያለው፤

፳፪(፬) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ ፷ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የዋስትና ገንዘብ በአክሲዮን ድርሻቸው መጠን ኢትዮጵያዊ በብር፤ ትውልደ ኢትዮጵያዊና የውጭ ሀገር ዜጋው በውጭ ምንዛሬ በዝግ ሒሳብ በባንክ የሚያስቀምጡ ይሆናል፡፡"

10/ The following new Sub-Articles (3) and (4) are added after Sub-Article (2) of Article 22 of the Proclamation and the existing Sub-Article (3) is re-numbered as Sub-Article (5)

"22(3) Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article Ethiopian Born foreign nationals or foreigners, can engage in overseas employment of skilled manpower, jointly with Ethiopian as agency:

a) the applicant is Share Company or Private Limited Company (PLC) or partnership and the members of the company with a share of 75 percent (Seventy Five Percent) from Ethiopian nationals 25 percent (Twenty Five percent) from Ethiopian Born foreign nationals whose equivalent value not less than 2(Two) Million Ethiopian Birr;

b) the applicant is Share Company or Private Limited Company (PLC) or partnership and the members of the company are with a share of 80 percent (Eighty percent) from Ethiopian nationals and 20 percent (Twenty percent) foreign nationals whose equivalent value not less than 2(Two) million Ethiopian Birr;

22(4) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) paragraph (a) and (b) Ethiopian born in Ethiopian Birr or Ethiopian born foreign nationals and foreign nationals in foreign currency, shall deposite the proclaimed guarantee fund under the Proclamation Article 60 Sub- Article (1) in a closed account opened for this purpose."

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

፲፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፡፡

"፳፫(፫) የጉዞ ወኪል እና የአየር መንገድ ትኬት ሽያጭ ቢሮ ወይም የወኪሉ ወይም የቢሮው ሠራተኛ ትራንዚተር፤"

፲፪/ የአዋጅ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተተክቷል፡-

"፳፬(፯) የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሮት ስለ ትምህርት ዝግጅቱ እና የሥራ ልምዱ እንዲሁም ሌሎች ሠራተኞችን በተመለከተ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡"

፲፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፲) ተሰርዞ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (፲፩)፤ (፲፪) እና (፲፫) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፲)፤ (፲፩) እና (፲፪) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

፲፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፯ ተሰርዞ በአዲስ አንቀጽ (፴፯) ተተክቷል፡-

"፴፯/ __የሥራ ውልን ስለማፅደቅ__

፩) መንግስት ለመንግስት፣ በኤጀንሲና በግል ጥረት ለሚደረግ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ሚኒስቴሩ ያወጣውን ሞዴል የሥራ ውል መሠረት በማድረግ የዜጋን መብት፣ ክብርና ደህንነት የሚያስከብር የሥራ ውል ተዘጋጅቶ በአሠሪ፣ ሠራተኛና እንደአግባብነቱ በኤጀንሲ ተፈርሞ በሚኒስቴሩ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

11/ Sub-Article (3) of Article 23 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (3).

"23(3) Travel agency and airlines ticket office or agent or employee of the the office transitor;"

12/ Sub-Article (7) of Article 24 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (7):

"24(7) Proof of documents that the general manager has at least first degree in his educational background and required years of experience and documents concerning other staff of the agency shall be specified by the Directive to be issued by the Ministry."

13/ Sub-Article (10) of Article 24 of the Proclamation is deleted and previous Sub-Articles (11), (12) and (13) are re-numbered as Sub-Articles (10), (11) and (12).

14/ Article 37 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 37:

"37/ __Approval of Contract of Employment__

(1) For overseas employment facilitated through Government to Government, private employment agency or direct recruitment, a contract of employment should be drawn based on the model employment contract provided by the Ministry to ensure the protection of Ethiopian migrant workers' rights, dignity and safety and must be approved by the Ministry after it is signed by the employer, the worker and by the agency as appropriate.

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

፪/ አሠሪ ወይም ኤጀንሲ የሥራ ውልን ለማጽደቅ በህግ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት አግባብ ላለው ባለስልጣን በማቅረብ ይሁንታ ካገኘ በኋላ ለሚኒስቴሩ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫) ሚኒስቴሩ የዜጋው መብት ደህንነትና ክብሩ ተጠብቆ የሚሰራ መሆኑን በማረጋገጥ እንደሁኔታው አግባብ ላለው ባለስልጣን የሥራ ውል ማጽደቅን በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡"

፲፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሐ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሐ) ተተክቷል፡፡

"፵፪(፪)(ሐ) አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያልያዘ ሠራተኛ መመልመል፡፡"

፲፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ከ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ከ) ተተክቷል፡፡

"፵፪(፫)(ከ) ከምልመላ በፊትም ሆነ የቅድመ ስምሪት ሥራ ተጠናቆ ውል ከፀደቀ በኋላ በማናቸውም ሁኔታ የሠራተኛውን ሕጋዊ የጉዞ ሰነዶችን ይዞ ማቆየት ወይም መከልከል፡፡"

2/ An employer or an agency may submit contract of employment to the Ministry for approval once the requirements specified in law are fulfilled and the documents have been reviewed and verified by the appropriate Authority.

3/ The Ministry may delegate the authority of approving contract of employment to an appropriate authority that safeguard citizen's rights, safety and dignity."

15/ Paragraph (c) of Sub-Article (2) of Article 42 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new paragraph (c) of Sub-Article (2).

"42 (2)(c) Recruiting a worker who does not possess certificate of occupational competence from an authorized center."

16/ Paragraph (q) of Sub-Article (3) of Article 42 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new paragraph (q) of Sub-Article (3).

"42(3)(q) Withholding or prohibiting the travel documents and other information of worker before recruitment or after the completion of pre-deployment process and the approval of the employment contract."

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

፲፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ወ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ዐ) ተጨምሯል፡፡

"፵፪(፫)(ዐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ከ) የተደነገገው ቢኖርም ኤጀንሲው በእጁ የሚገኙ የሠራተኛው ህጋዊ የጉዞ ሠነዶች ሠራተኛው እንዲመለስለት ሲጠይቅ በአንድ ሰዓት ውስጥ አለመስጠት፤"

፲፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፵፫(፩) ማንኛውም ተጎጂ ሠራተኛ ወይም የተጎጂው ሠራተኛ ተወካይ ወይም የተጐጂ ሠራተኛ ቤተሰብ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ሌላ ተዛማጅነት ያለው ሕግ በኤጀንሲው ተጥሷል በሚል ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን አቤቱታ በጽሁፍ ወይም በቃል ማቅረብ ይችላል፡፡"

፲፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡፡

"፶፱(፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በፍሬ ነገር ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡"

፳/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡-

"፷፩(፪) ማንኛውም የውጭ ሀገር አሠሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር ለተጠቀሰው ዓላማ የሚውል ለቀጠረው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ አንድ መቶ (፻)

17/ The following New paragraph (t), is added after paragraph (s) of Sub-Article (3) of Article 42 of the Proclamation is added.

"42(3)(t) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3), paragraph (q), failing to return travel documents within one hour upon receiving the request from the worker."

18/ Sub-Article (1) of Article 43 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1).

"43(1) Any victim worker or his representative or family member may submit oral or written complaint to the Ministry or appropriate authority when this Proclamation or any Regulation or Directive issued here under or any other relevant law has been infringed by an agency."

19/ Sub-Article (2) of Article 59 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2).

"59(2) The decision given by Court of law regarding the issue of fact, pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be final."

20/ Sub-Article (2) of Article 61 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2).

"61 (2) Any foreign employer shall deposit United States Dollar(USD) 100 per worker to the Foreigner Employers' Guarantee fund established by this

Scanned with ScannerMaster

Scanned with CamScanner

የአሜሪካን ዶላር በአዋጁ መሠረት ለተቋቋመው የውጭ አሠሪዎች ዋስትና ፈንድ መዋጮ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡”

፳፩/ ከአዋጁ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፡-

“፷፩(፫) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የውጭ አገር አሠሪ በሥራ ውል መጣስ ምክንያት ለሚደረግ ክፍያ የሚውል ለውጭ አሠሪዎች ዋስትና ፈንድ የሚያስገባው የመዋጮ መጠን እንደገበያው ሁኔታ እየታየ ሚኒስቴሩ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡”

፫/ <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳፮ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

Proclamation, for the purposes specified under Sub-Article (1) of this Article."

21/ The following new Article (3) is added following Sub-Article (2) of article 61 of the Proclamation.

"61(3) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the amount of money to be deposited by foreign employer for the purpose of covering claims of workers that may arise from breach of contract of employment may be revised by a Directive to be issued by the Ministry, depending on the prevailing market conditions. In consultation with Ministry of Finance."

3/ <u>Effective date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 3rd day of June, 2021.**

**SAHLEWORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

Scanned with ScannerMaster



Scanned with CamScanner